የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 40
ADDIS ABABA 12th May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፲፮/፪ሺ፫

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..............ገፅ ፭ሺ፰፻፳፪

**CONTENTS**

**Regulation No. 216/2011**

Addis Ababa Science and Technology University Establishment Council of Ministers Regulation.......... Page 5822

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፮/፪ሺ፫

### የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፮/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. መቋቋም**

፩/ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 216/2011

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN CONFORMITY ASSESSMENT ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa Science and Technology University Establishment Council of Ministers Regulation No. 216./2011".

**2. Establishment**

1/ Addis Ababa Science and Technology University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫. **ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል።

፬. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

3. **Main Campus**

The University shall have its main campus in Addis Ababa and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 12th day of May 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት